# በቅናሽ ዋጋ አፓርታማ መከራየት ይፈልጋሉ?

## ስለዚህ ሀብት ይወቁ።

አመልካቾች በቤተሰባቸው መጠን ላይ ተመስርተው ለቅናሽ ዋጋ ክፍሎች ሎተሪ ውስጥ መግባት ይችላሉ። የዲሲ መንግስት በብዙ አዳዲስና የታደሱ የአፓርታማ ህንጻዎች ላይ ከ 8-10% የሚሆኑት ክፍሎች በቅናሽ ዋጋ እንዲከራዩ ይጠይቃል።

ይህ ፕሮግራም አካታች የዞን ክፍፍል ፕሮግራም (IZ) ይባላል እና የቀረበው በመኖሪያ ቤቶችና የማህበረሰብ እድገት ክፍል (DHCD) ነው። እንዲሁም ይህ ፕሮግራም ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸውን ክፍሎች ለሽያጭ ያቀርባል።

## ብቁ መሆንዎን ያጣሩ።

እነዚህ **ሁሉ** መግለጫዎች እውነት ከሆኑ ብቁ ነዎት ማለት ነው፡

- እንዲሁም የሙሉ ጊዜ የኮሌጅ ወይም የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ከሆኑ፣ የቤተሰብ ገቢ መግለጫን የሚያሟላ ቤተሰብ ያለው ሰው ላይ ጥገኛ መሆን አለብዎት።
- የቤተሰብዎ አመታዊ **አጠቃላይ ገቢ—ታክስ ከመክፈልዎት በፊት ያለው ገቢዎ— የቤተሰብዎ መጠን ዝቅተኛውና ከፍተኛው ገደቦች መካከል ነው**። ይሁን እንጂ፣ እንደ ኪራይ ቫውቸር ወይም ድጎማ ያሉ የኪራይ እርዳታ ከተቀበሉ ዝቅተኛ መስፈርት የለም። የቤተሰብዎን ገቢ ለማስላት፣ ከታክስ በፊት እያንዳንዱ በቤተሰብዎ ውስጥ ያለው ሰው ሰርቶ ወይም ከሌላ ምንጮች የሚያገኘውን ብር ይደምሩ። ከዚህ በታች ምልክት ያድርጉ።

| **የቤተሰብ መጠን** (ደባሎችን ጨምሮ ከእርስዎ ጋር የሚኖሩትን ማንኛውም ሰዎች ይቁጠሩ) | **ትንሹ የቤተሰብ ገቢ** (የኪራይ እርዳታ የሚያገኙ ከሆነ ዝቅተኛ የገቢ መስፈርት የለም) | **ከፍተኛው የቤተሰብ ገቢ ገደብ** |
|---|---|---|
| 1 | ስቱዲዮ - $25,200<br>1 መኝታ - $27,100 | $70,550 |
| 2 | ስቱዲዮ - $25,200<br>1 መኝታ - $27,100<br>2 መኝታ - $32,650 | $80,650 |
| 3 | 1 መኝታ - $27,100<br>2 መኝታ - $32,650<br>3 መኝታ - $37,900 | $90,700 |
| 4 | 2 መኝታ - $32,650<br>3 መኝታ - $37,900<br>4 መኝታ - $43,200 | $100,800 |
| 5 | 2 መኝታ - $32,650<br>3 መኝታ - $37,900<br>4 መኝታ - $43,200 | $110,900 |
| 6 | 3 መኝታ - $37,900<br>4 መኝታ - $43,200 | $120,950 |
| 7 | 3 መኝታ - $37,900<br>4 መኝታ - $43,200 | $131,050 |
| 8 | 3 መኝታ - $37,900<br>4 መኝታ - $43,200 | $141,100 |

ለማመልከት የዲሲ ነዋሪ ወይም ዲሲ ውስጥ የሚሰራ ሰው መሆን አይጠበቅብዎትም። ነገር ግን በደንቦቹ መሰረት የዲሲ ነዋሪ ለሆኑ ወይም ዲሲ ውስጥ ለሚሰሩ ቤተሰቦች ፕሮግራሙ ቅድሚያ መስጠት አለበት።

# ያመልክቱ።

1. ይመዝገቡ እና የ IZ የገለጻ መስጫ ክፍልን (IZO) ያጠናቅቁ።
2. ለ IZ የሎተሪ ማሳወቂያ ኢሜይሎችይመዝገቡ። ለመመዝገብ የ IZ የገለጻ መስጫ ክፍል የምስክር ወረቀት ያስፈልግዎታል። ወደ ዝርዝሩ እንደታከሉ የሚያረጋግጥ ኢሜይል ይደርስዎታል።

በማንኛውም ጊዜ ማመልከት ይችላሉ።

# ተጨማሪ መረጃ ይሰብስቡ።

### ካመለከትኩ በኋላ ምን ይፈጠራል?

1. ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ ብለን ያሰብንበት የ IZ ክፍል በተገኘ ጊዜ ሁሉ፣ እርስዎ ኢሜይሎችን መቀበል ይጀምራሉ።
2. ለመከራየት ፍላጎት ያሳደረብዎት የ IZ ክፍል ሲያዩ፣ ለዛ ክፍል ሎተሪ ውስጥ ይግቡ። በኢሜይልዎ በተላከው መገናኛ በኩል ወደ ሎተሪው መግባት ያስችልዎታል።
3. በመደበኛነት አስር ቤተሰቦች በሎተሪው ውስጥ በዘፈቀደ ይመረጣሉ እና ከ 1-10 ደረጃ ይሰጣቸዋል። በሎተሪ ውስጥ ከተመረጡ፣ እንዴት እንደሚያመለክቱ ያሉ ዝርዝሮችና የመጨረሻዎቹ ቀናት ጋር ኢሜይል ይደርስዎታል።

የኪራይ ሂደቱን ከጀመሩና ብቁ እንዳልሆኑ ከቆጠሩ፣ የእርስዎ ቤተሰብ የገቢ መስፈርቱን እስካሟላ ድረስ አሁንም የወደፊት ሎተሪዎች ላይ መሳተፍ ይችላሉ።

### ሁሉም ብቁ አመልካቾች ክፍል ለመከራየት እድሉን ያገኛሉ?

አይ። በየአመቱ ወደ 150 IZ ክፍሎች የሚሆኑ ለኪራይ ይገኛሉ እና በማንኛውም ጊዜ በግምት ወደ 10,000 የሚሆኑ ቤተሰቦት የ IZ ክፍሎችን ለመከራየት ፍላጎት አላቸው። ቤተሰቦች የሚመረጡት በሎተሪ ነው።

### ማወቅ ያሉብኝ ተጨማሪ መስፈርቶች አሉ?

የ IZ ክፍሎች ከተከራዩ፣ በየአመቱ የቤተሰብዎን የገቢ ዶክመንቶች ዳግም ማስገባት አለብዎት እንዲሁም ቤቱ ለእርስዎ ዋና መኖሪያ እንደሆነ ማረጋገጥ አለብዎት። ለቤተሰብዎ መጠን፣ ገቢዎ እስከ 1.4 ጊዜ በአመቱ እስካለው ከፍተኛ የሚፈቀድ ገቢ ድረስ ሊወጣ ይችላል። በሂደቱ ላይ ከህንጻ ንብረት ሃላፊው ጋር ይሰራሉ።

### ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማነጋገር ያለብኝ ማንን ነው?

መጀመሪያ፣ በገጹ የታችኛው ስፍራ ላይ ያለውን በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች የሚለውን ይመልከቱ። አሁንም ጥያቄዎች ካሉዎት የእኛን አካታች የዞን ክፍፍል ቡድን በ 202-442-7221 ላይ ከሰኞ - አርብ ከ 8:15 am እስከ 4:45pm ባለው ጊዜ ውስጥ ይደውሉ። ወይም በiz.adu@dc.gov ላይ “Inclusionary Zoning Question” በሚለው ርዕሰ መስመር በመጠቀም ለቡድኑ ኢሜይል ያድርጉ።

**አሁንም ለመኖር ዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ ቦታ እርዳታ እፈልጋለሁ። ምን ማድረግ አለብኝ?**
በእኛ ጊዜያዊ የመኖሪያ ቤት ገጽ ላይ እርዳታ ሊሰጡ ስለሚችሉ ሌሎች ሀብቶች መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

**በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች**
**ከዚህ ፕሮግራም ጋር ቮውቸር ወይም ድጎማ መጠቀም እችላለሁ?**
አዎ፡ የኪራይ ቮውቸሩ ወይም ድጎማው ከአሁን የመኖሪያ ስፍራ ወደ ሌላ ከተንቀሳቀሰ፣ የእርስዎን የ IZ ክፍል ኪራይ ለመክፈል እንዲረዳዎ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። አከራዩ በ DHCD ከተዘረዘረው ከፍተኛ የ IZ ኪራይ በላይ ማስከፈል አይችልም።

**የገለጻ መስጫ ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት አገልግሎቱ ሊያበቃ ይችላል?**
አዎ፣ የምስክር ወረቀቱ ከሁለት አመት በኋላ አገልግሎቱ ያበቃል። የ IZ ምዝገባዎን ለማደስ፣ የምስክር ወረቀትዎ ጊዜው ከማለቁ **በፊት** የገለጻ መስጫ ኮርስ እንደገና መውሰድ አለብዎት። እንደገና ኮርሱን ከወሰዱ በኋላ፣ አዲሱን የምስክር ወረቀት ኮድና የማንኛውም የቤተሰብ አባል ወይም የገቢ ለውጦችን ወደ iz.adu@dc.gov ኢሜይል ማድረግ አለብዎት። የምስክር ወረቀትዎ የአገልግሎት ጊዜው ሊያበቃ ሲል ማሳወቂያ ላይደርስዎት ይችላል ስለዚህ ማስታወሻ እንዲያዘጋጁ እናበረታታዎታለን።

**በዚህ ፕሮግራም ውስጥ አፓርትመንት ለመከራየት ከጀመርኩ በኋላ ገቢዬ ቢለወጥስ?**
አንዳንድ የገቢ ጭማሪዎች ተፈቅደዋል። የኪራይ ውልዎን ለሌላ አመት ከማደስዎ በፊት፣ የቤተሰብዎ ገቢ አሁንም በመስፈርቶቹ ውስጥ እንደገባ ከንብረት ሃላፊው ጋር ማረጋገጥ አለብዎት። ይህ ካልሆነ፣ እንደገና ማደስ አይችሉም። የንብረት ሃላፊው መመሪያዎችን ይሰጥዎታል።

**የ IZ ክፍል ለመከራየት እድሉን ባገኝ፣ መከራየት አለብኝ?**
አይ፣ በቀላሉ ፍላጎት እንደሌለዎት ለንብረት ሃላፊው መናገር ይችላሉ። የወደፊት ሎተሪ ኢሜይሎች መቀበልዎን ይቀጥላሉ።

**የ IZ ክፍል ከዚህ በፊት ተከራይቼ ከሆነ እንደገና ማመልከት እችላለሁ?**
አዎ። ዳግም ሊያመለክቱ ይችላሉ ነገር ግን በአንድ ጊዜ አንድ ክፍል ብቻ መከራየት ይችላሉ።

*ይህ ገጽ ለመጨረሻ ጊዜ የተሻሻለው ሜይ 2021 ነው።*